
## በመጽሔቱ ውስጥ የተገለጡት አርእስቶች ፤


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ፩· መግቢያ | ፫—፬ |
| ፪· ፓትርያርኩ የልደትን በዓል ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት ቃለ በረከት | ፭ |
| ፫· የጥምቀት በዓል በየዓመቱ ለምን ይከበራል ? | ፮—፰ |
| ፬· የኢትዮጵያ በዓለ ጥምቀት በውጭ አገር ተመልካቾች ዘንድ | ፱—፲ |
| ፭· የመጀመሪያው ተአምር በሠርግ ቤት | ፲፩—፲፪ |
| ፮· መንፈሳዊ ደስታ በቅዱስ ጋብቻ | ፲፫—፲፭ |
| ፯· የእግዚአብሔር መኖር በሥነ ፍጥረቱ ይታወቃል | ፲፮—፲፯ |
| ፰· ምሥጢረ ንሥሐ | ፲፰ ፳ |
| ፱· ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደመወዛቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ስለ መፍቀዳቸው ለቀረበላቸው ጋዜጣዊ ጥያቄ የሰጡት መልስ | ፳፩—፳፪ |
| ፲· መልካም አርአያነት | ፳፫—፳፬ |
| ፲፩· ተናገሩ አበው | ፳፭—፳፮ |
| ፲፪· የትኛውን ልምረጥ | ፳፯—፳፰ |


በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ፡ ቤት ታተመ ።

# ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
ደመወዛቸውን ለቤተ ክርስቲያን



1/69

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለበዓለ ጥምቀት በተቋቋመው በትምህርትና በድራማ ፣ በሥነ ሙዚቃና በሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጀ ።

ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም.

# ፓትርያርኩ የልደትን በዓል ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት ቃለ በረከት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

በነገው ዕለት ሁላችንም በታላቅ ደስታ የምናከብረውን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በከተማና በገጠር ላላችሁ ምእመናን ሁሉ፥እንኳን ለዚህ ዕለት በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ በቅድሚያ የመልካም ምኞት መልእክት አስተላልፋለሁ ።

የሰላም አምላክ ሁላችንንም በቸርነቱ ጠብቆ ይህንን የደስታ ዕለት ለማክበር ስላበቃን ስሙ የተመሰገነ ይሁን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም የተወለደ የሰላም አምላክ በመሆኑ በዓለ ልደቱን በየዓመቱ በታላቅ ደስታ በምናከብርበት በዚህ ዕለት በከፍተኛ ስሜት ልናስታውሰው የሚገባ አንድ ዓቢይ ነገር አለ ።

ይኸውም ይህ አሁን በዓለም ላይ ጎልቶ የሚታየው በሰውና በእግዚአብሔር እንዲሁም በሰወች መካከል ያለው መልካም ግንኙነት የተመሠረተው በክርስቶስ መሆኑን ነው ።

በመጀመሪያው ሰው ስሕተት ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ተደቅኖ የነበረው የጥል ግድግዳ የፈረሰው በክርስቶስ ነው ።

እንደዚሁም በምድር ላይ ትክክለኛው የሆነ የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓት ይታነጽ ዘንድ በመጀመሪያ መሠረት የተጣለው በክርስቶስ መወለድ ነው ።

ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የሰማይ ሠራዊት ሁሉ «ምስጋና ለእግዚአብሔር በአርያም ፤ ሰላምም በምድር ይሁን» የሚል የደስታ መዝሙር ያሰሙትም ስለዚህ ነበር።

በክርስቶስ መወለድ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን በቅተናል ። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ዘንድም ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም የምንችል የምግባርና የሃይማኖት ሰዎች ሆነናል ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ «እግዚአብሔር ዓለሙን ስለወደደ አንዱን ልጁን ወደ ዓለም ላከ» ይላል ። በእርግጥ ቃል ሥጋ የሆነውና የእግዚአብሔር ልጅ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው የሰውን ልጅ ከኃጢአት ሞት ለማዳን ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ምድራዊ ኑሮ ጠቃሚ የሆኑትን ኅብረትንና እኩልነትን እውነተኛ ፍቅርንና ሰላምን ለማስተማር ነው ።

ፍቅርና እኩልነት በሰወች መካከል ከሌለ ግን ሰላምም በምድር ላይ ሊኖር አይችልም ።

ስለዚህ ክርስቶስ የፍቅርና የነጻነት ፤ የሰላም አምላክ በመሆኑ በየዓመቱ በዚህ ዕለት በዓለ ልደቱን ስናከብር ታላቅ ደስታ ይሰማናል ።

ሁላችንም ለዚህ ዕለት በሰላም ያደረሰን አምላክ ለሚመጣውም ዓመት በሰላም አድርሶን ይህን ታላቅ በዓል በደስታ ለማክበር ያብቃን ።

# የጥምቀት በዓል በየዓመቱ ለምን ይከበራል?

ይህ ዓይነቱ ጥያቄ በየጊዜው እየተደጋገመ የሚጠየቅና የተለመደ ጥያቄ ነው ። በተሳሳተ መንገድም ሆነ ፣ በትክክለኛው መንገድም የተለያዩ መልሶች ሳይሰጡበት የቀረ አይደለም ።

ትውልዱ ነገዱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ የውጭ ዜጋ እግር ጥሎት በጥምቀት ወራት ኢትዮጵያን በሚጎበኝበት ጊዜ በዓሉ ክፍ ባለ ሥነ ሥርዓት በደመቀ ሁኔታ ሲከበር ፤



በየወንዙ ዳር ታቦታቱ ወርደው፣ሲቀደስ፣ሲወድስ ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑም ከጸሎቱ ሥነ ሥርዓት በኋላ ውሀ ሲረጩ፣ከዚህ ጋራም ወንዱ በሆታ ሴቱ በእልልታ በዘፈኑ በጨዋታ የደስታ ስሜታቸውን ሲገልጡ፣ቢያይ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ጥምቀታቸውን ወይም



ክርስትናቸውን ያድሳሉ በማለት ይገምታል ። የተሳሳተውን አስተያየቱንም ይሰጣል ። አባባሉ ግን ከውነት የራቀ ነው፤ልደተ ነፍስና ልደተ ሥጋ ሁለቱ ልደታት ለሚወለደው ሁሉ ከፍተኛ ጥቅም አላቸው ። ሰው ካልተወለደ አለኝታ የለም ። አለኝታም ከሌለው ወራሽ ቀራሽ መሆን አይችልም ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው ፤ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል» በማለት አስፈላጊነቱን ይናገራል ። ዮሐ ፫ ፮ ለሰው በተሰጠው ሥጋዊ ጥበብ ብዙ አዳዲስ ነገሮች ይፈለሰፋሉ ። ከጊዜ በኋላም ያረጃሉ ። ሆኖም በአንድ ጊዜ አይጣሉም ፤ ያረጀው ይታደሳል የተሰበረው ይጠገናል ። ተመልሶ የማይመጣ ልጅነት ብቻ ነው ፤ ሰው ካረጀ ካፈጀ በኋላ ወደ አባቱ አብራክ ተመልሶ ወደእናቱ ማኅፀን ገብቶ ዳግመኛ መወለድ አይችልም።እንደዚሁም ሁሉ ሰው መጠመቁ በአዲስ ልደት ልደተ ነፍስን ለመወለድ ነው። ይህከውሀና ከመንፈስ የምንወለደው ልደት ከእናት ከአባት ለምንወለደው ለልደተ ሥጋ ዳግም ልደት ቢባልም አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ሁለተኛ የማይደገም ምሥጢር ነው ።

ክርስትና በተሰበከበት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች ሥር ዓት ቢያፋልሱና እንደገና እንጠመቅ ቢሉ ቅዱስ ጳውሎስ «መሠረትን ደግመን አንመ ሥርት፤ እርሱም ስለጥምቀትና እጅችንም ስለመጫን ነው » ። ነገር ግን ጥምቀትን ከተቀበሉ በኋላ ከሰማይ የሚሰጥ ጸጋውን ከቀመሱ በኋላ በመንፈስ ቅዱስም አንድ ከሆኑ በኋላ አይቻልም» ማለቱ የሚታመን ነው ። ዕብ ፮ ፩—፬ ። ስለዚህ የዚህን ንባብ ከትርጓሜው ኃይለ ቃሉን ከምሥጢሩ ጋር አመሣጥራ የምታውቀውና ከሥራም ላይ ያዋለችው ስለሆነች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ ጥምቀትን ለማደስ ወደወንዝ አትወርድም ። ኃጢአት በሚሠረይበት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን እናሳምናለን ። ይህ የሃይማኖታችን መሠረት ነውና ። ርግጥ ነው አምነው ተጠምቀው በክርስትና ጸን ተው ከኖሩ በኋላ በኃጢአት የሚሰነካከሉትን ተነሳሕያን ለንስሓ የሚያበቃ ሥራ እን ዲሠሩ ታደርጋለች።ይኸውም በዓመት አንድ ጊዜ የጥምቀት ዕለት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተግባር አድርጋ የያዘችው የዘወትር ሥራዋ ነውና፣ ምእመናን ሁሉ በምክረ ካሁን በፈ ቃደ ካህን እንዲኖሩ ታደርጋለች ።

ከኢትዮጵያ ውጭ ሌሎች አገሮች ብሔር አቀፍ አድርገው የሚያከብሯቸው ልዩ ልዩ በዓላት አሏቸው ። እነዚህም ወራትን ተከትለው የሚከበሩ ናቸው ። የልምላሜው ወራት አልፎ የአበባው ወራት ሲተካ የአበባ በዓል የሚከበርበት አገር አለ ። የእግዚ አብሔርን ከሀሊነትና ቸርነት ለመግለጽ (ታንክስ ጊቪንግ ደይ)የምስጋና ማቅረቢያ ቀን ተብሎ መንፈሳዊ በዓል የሚከበርባቸው አገሮች ም አሉ ። የእግዚአብሔር የበኵር ልጅ የተባሉ እስራኤል መከሩን ማጨድ ከጀመሩበት ቀን ጀምረው ሰባት ሱባኤ ቈጥረው በዓለ ሰዊትን ሲያከብሩ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ደስታቸውን ይገልጹ ነበር ።

በአገራችንም የአበባውና የፍሬው በዓል በመስከረም በጥቅምት ወራቶች ሲታሰብ ከመኖሩም ሌላ የጥምቀትን በዓል ወይም ክብረ ቅዱሳንን ምክንያት በማድረግ በዚህ በጥር ወር ሰው ሁሉ እንደየአቅሙ ከፍ ያለ ዝግጅት ያደርጋል ። የክቱ የሚወጣው ያማረ ልብስ የሚለበሰው በዚህ ጊዜ በመሆኑ «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» እየተባለ ይነገራል ። በዚህ መልክ የሚከበረው ብሔራዊ የጥምቀት በዓል ጥንቱ ወይም መሠረቱ መንፈሳዊቢሆንም፣በተጨማሪምወራቱ የመካተቻ ወራት ነው ። ዓመት ሁሉ የተደከመ በት እህሉ የሚሰበሰበው፣መከሩ የሚከተተው በአብዛኞቹ ክፍላተ ሀገር በዚህ በጥምቀት ወራት ሲሆን የወደፊቱ የእርሻው ጊዜም ወቅቱ ወራቱ ገና ስላልደረሰ ሠራተኛው ነጻ ይሆናል ። አዎን! «የሚያጭድ ደመወዙን ይቀበላል፤የሚዘራና የሚያጭድም አብረው

ደስ እንዲላቸው የዘለዓለም የሕይወት ፍሬን ይሰበሰባሉ» የሚለው የክርስቶስ ትምህርት ሰም ለበስ ሆኖ ያቀረበው ይህን የመሰለውን የሰው ልጅ ተግባር ሲገልጽ ነው ።

ክቢሮው የሚሠራው የመንግሥት ሠራተኛ ሕጋዊ የዓመት ፈቃዱን ባሻው በፈለገው ጊዜ ወስዶ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያርፍ ሕግ ይፈቅድለታል ። አራሹ ገበሬ ታታሪው ባላገር ግን የዓመት ዕረፍት የሚያገኘው ባሕልንና እምነትን ተደግፈው በሚመጡ ወራቶች ነው ። ስለህ ይህ የጥምቀት ወራት ሰው ሁሉ አንድ ሆኖ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ያሚያቀርብበት አንድ ሆኖ ደስታውን የሚገልጽበት ወራት ነው ።

በርግጥ በደመቀ ሁኔታ በየዓመቱ የሚከበረው የጥምቀት በዓል እምነትን የተከተለ፥ ታሪክን የተመረኰዘ ነው ። ዮሐንስ መጥምቅ ሥራ የጀመረ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ እንደነበረ ይታመናል ። የዮሐንስም ሥራ ሕዝቡን ለንስሐ ማዘጋጀትና የተዘጋጀውንም ሕዝብ የንስሐን ጥምቀት ማጥመቅ ነበረ ። በዚህ መሠረትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነገ ሊጠመቅ ከዋዜማው ጀምሮ ሕዝቡ በብዛት ተሰብስቧል ። የከተራው በዓል መነሻ ይህ ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወግ፥ ታሪክ በመጠበቅ ከከተራ ጀምሮ ወደወንዝ በመውረድ የጥምቀትን በዓል መታሰቢያ በየዓመቱ ታከብራለች ።

በሌላም በኩል ይህ የጥምቀት ወራት ኤጲፋኒ ወይም አስተርእዮ የሚል ስያሜ ሲኖረው ትርጓሜውም መገለጫ ማለት ነው።የሰው ፍቅር አገብሮት ራሱን ዝቅ አድርጎ የተገለጠ ክርስቶስ የባሕርይ ልጅነቱን የገለጠበት ወራት ነውና ። ወንጌላውያን የልደቱን ወግ ታሪክ በተለያየ አቀራረብ እንደገለጹ ይታወሳል ። ወንጌላዊው ሉቃስ ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ስብእን ሲፈጽም አደገ በማለት ሲያብራራ በስምንት ቀን ተገዘረ ። በአርባ ቀን ዕጉለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ቤተ መቅደስ ገባ ለዘመዶቹና ለእናቱ እየታዘዘ በጥበብ በጸጋ በሞገሥ አደገ ማለቱ የሚታበል አይደለም ።

ሠላሳ ዓመት ሲሞላው ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ተገለጠ ። በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ በዚህ ጊዜ ወልድ በክበበ ትሰብእት ማለት በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ሲገለጥ አብ በደመና ሆኖ የምወደው የምወልደው ይህ ልጄ ነው ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት የሥላሴ ሶስትነታቸው ታወቀ ተረዳ ። ይህ ሁሉ ሲፈጸም አይቶ ዮሐንስ መጥምቅ ሲመሰክር «እኔም አይቻለሁ ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ» ብሎ በግልጥ ተናገረ ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን የቅዱስ ወንጌልን ትምህርት ተከትላ (በሃይማኖተ ርዕይ የሃይማኖተ ሰሚዕን) ምሥጢር አስተካክላ የጥምቀትን ወራት ዘመነ አስተርእዮ ብላ ታከብራለች እንጂ ጥምቀትን በየዓመቱ አታድስም ።

አባ መዓዛ ቅዱሳን ገ/ ሕይወት ፤



# የኢትዮጵያ ብዓለ ጥምቀት በውጭ ሀገር ተመልካቾች ዘንድ

ከመርዓዊ ተበጀ

አገራችን ኢትዮጵያና ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን በከፍተኛ ደረጃ የሚያከብሯቸው ዐበይት በዓላት ብርከት ያሉ ቢሆኑም ከነሱ ውስጥ ግን እጅግ ድምቀትና ውበት ያለው በዓላችን በርእሱ የተጠቀሰው በዓለ ጥምቀት ነው። በብሔራዊ ልማዳችን የሕዝቡም አባባል «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» የሚል ነው ፤ ይህም ካሉት በዓላት ሁሉ ጥምቀት ከፍተኛ በዓል መሆኑን ሲያበስር በበዓልነቱ ብቻ ሳይሆን በፍሬ ነገሩም አንድነትና ሦስትነት የተገለጸው በጌታ ጥምቀት ስለሆነ እጅግ የጋለ መንፈሳዊ ስሜት ያለበት በዓል መሆኑ የሚታወስ ነው ። ሰው በእግዚአብሔር አብ ፤ በእግዚአብሔር ወልድ ፤ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፤ ስም ካልተጠመቀ የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን አይችልም ። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመካፈል የግድ ጥምቀት ያስፈልጋል ።

በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች በአንዳንድ መሠረተ ሀሳብ ቢለያዩም በጥምቀት ግን አንድ ናቸው ሁሉም «ጥምቀት አንዲት» እንደሆነች ይመሰክራሉ መመሪያቸውም ሀዋሪያው ቅ/ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው በም-፬ በቁ ፬-፭ ያለው «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ ፤ አንድ ጌታ ፤ አንድ ሃይማኖት ፤ አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ ፤ በሁሉም የሚኖር ፤ አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ » ብሎ የተናገረው ነው ።

በዚህ አኳኋን አንድ ጊዜ የተጠመቁት ጥምቀት በምንም ምክንያት አይመለስም አይከለስም ፤ ጥምቀት የማያረጅ የማያፈጅ በዘመን ብዛት የማይለወጥ ነው ፤ ምክንያቱም ጥምቀት የሚፈጸመው በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነውና ። እራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ፤ የባሕርይ ልጅነቱን በአብና በመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮ ፤ ሰማያዊ ተልእኮውን ከፈጸመ በኋላ ወደ ሰማይ በሚያርግበት ጊዜ የተናገረው አምላካዊ ቃል «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ፤ አጥምቁአቸው በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም» የሚል ነው ። (ማቴ ፳፰-፲፱)

የኢትዮጵያ በዓለ ጥምቀት በውጭ አገር ተመልካቾች ዘንድ ወደሚለው ርዕሰ ነገር ስንገባ አሁንም የጥምቀትን አለመመለስና አለመከለስ ፤ አለማርጀትና አለማፍጀት ማወቅ ግድ ይሆንብናል ። ይህም ከላይ የተጠቀሰው የቅ/ጳውሎስ ቃል ሲሆን ፤ በተጨማሪም በሁሉተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በ፫፻፹፩ ዓ/ም አቡሊናርዮስንና መቅዶንዮስን ለማውገዝ የተሰበሰቡ ፤ ፩፻፶ የሚሆኑ ሊቃውንት የወሰኑትን ፤ እኛም በዘወትር ጸሎታችን የምናምነውን «ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርዩተ ኃጢአት ለኃጢአት ስርዬት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» የሚለውን የሃይማኖት ጸሎት ነው።»

ነገር ግን የሚያሳዝን ነገር ቢኖር የእኛን መመሪያ ያላወቁ ፤ የቤተ ክርስቲያናችንን ሥነ ሥርዓት ያልጠነቀቁ የውጭ አገር ሰዎች (አገር ጎብኝዎች) ስለ በዓለ ጥምቀት ያለውን አከባበር ቢያደንቁም ሁኔታው ስለማይገባቸው «ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ይጠመቃሉ ጥምቀትን ይመልሳሉ ይከልሳሉ እንደገና ይጠመቃሉ» ብለው የጻፉ አሉ ፤ ሆኖም ለዚህ ማስተባበያ የሰጠ ኢትዮጵያዊ ሊቅ እስካሁን ያለ አይመስለኝም ። የውጭ አገር ሊቃውንት ግን እርስ በርሳቸው ተመላልሰውበታል በቂ መረጃም አቅርበዋል ።

እንግዲህ ወደእነሱ አስተያየት እንመለስ ፤ አሁን ገና የተነሣሁበትን መሠረት ጥያቄ ለማቅረብ ከምፈልግበት ክፍል የደረስኩ ይመስለኛል ። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክር

ስቲያን መልዕክተኞች ወደአገራችን በ፲፫ተኛው ምዕት ዓመት ቢገቡም የካቶሊኮች በብዛት መግባት እጅግ ጎልቶ የሚታወቀው በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን ነው ፤ በዚህም ጊዜ የፖርቱጋል ካቶሊኮች ኢየሱሳውያን በብዛት ገብተዋል ። ከነርሱም ውስጥ በታሪክ ጸሐፊነቱ የታወቀው ፤ ኢትዮጵያን ከውጭ ዓለም ጋራ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥነ ጽሑፍ ያስተዋወቀው ፤ ጴጥሮስ አልባሬስ ነበር ፤ ይህ ሰው በ፲፭፻፲፩ ዓ/ም ገደማ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ለአጼ ልብነ ድንግል ባለሟል ሆኖ ሲኖር ፤ የኢትዮጵያን ታሪክ መጻፍ ጀመረ ። ሆኖም ባያመቱ ስለምናከብረው ብዓለ ጥምቀት ሲናገር «በኢትዮጵያ ጥምቀት ይመለሳል ይከለሳል» አለ በሁኔታው ሐተታ በመስጠት እንዲህ ይላል «የኢትዮጵያ ካህናት በጥምቀት ዋዜማ (ከተራ) በብዛት ተሰብስበው መላ ሌሊቱን ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ በጥምቀተ ባሕሩ ዙሪያ አደሩ ። ንጉሡም ከንግሥቲቱ ጋራ በመንፈቀ ሌሊት ወደ ባሕረ ጥምቀቱ በሰልፍ መጣ ፤ ሊቀ ጳጳሱ አባ ማርቆስም አጠመቃቸው ያን—ጊዜም የንጉሡ መምህር የሆነው ታላቅ አዛውንት ወደባሕረ ጥምቀቱ ገብቶ እስከ አንገቱ ተነከረ ፤ ቄሱም ወደእርሱ ዘንድ ሂዶ «በአብ ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሀለሁ» እያለ በራሱ ላይ ሦስት ጊዜ ውሀ አፈሰሰበት ፤ በጥምቀተ ባሕሩ ዙሪያ የነበሩት ሁሉ ሴቱም ወንዱም ፤ ትንሹም ትልቁም ካንገታቸው በላይ በውሀ ተጠመቁ ይላል ። ሌላው ታሪክ ጸሐፊ አልፎንስ ሜንዴዝ «በዚህ ዓይነት መላው የሮማን ካቶሊክ እምነት የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይጠመቁ ነበር ፤ ሁለተኛ አንጠመቅም ያሉ ካቶሊኮች ግን ከኢትዮጵያ ተባረሩ» ይላል። ሁኖም የእነሱን ከንቱ አጻጻፍ ለማፍረስ በዘመኑ የነበረው ፤ በኢትዮጵያ ጥናቱ የዓለም ሊቃውንት ያደነቁት ፤ ጀርመናዊው ኢዮብ ልዶልፍ ግን ስለ ኢትዮጵያ በዓለ ጥምቀት አከባበር ሲጽፍ «- - - ኢትዮጵያውያን ፈጽሞ ጥምቀትን አይመልሱም አይከልሱም ለሁለተኛ ጊዜ አይጠመቁም ነገር ግን የክርስቶስን ጥምቀት በማስታወስ በዓለ ጥምቀትን በየዓመቱ ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ያከብራሉ» ብሎአል ይህንንም አስተያየት «የኢትዮጵያ መንፈሳዊ አገልግሎት» በሚለው መጽሐፉ የጻፈው ሩሲያዊው ኤጲስ ቆጶስ ጵርፊሪ ኡስፔን እስኪ ነው ።

ሌላው አራት ጊዜ ወደኢትዮጵያ የተመላለሰው ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፰፻፺፰ ዓ/ም ወደ አገራችን የመጣው ሩሲያዊው የጦር መኮንን እስክንድር ከሳቤሪቢች ቡላቶቢች ጥምቀት በኢትዮጵያ የማይመለስ የማይከለስ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ምስጢረ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል ። «ጥቂቶቹ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ እንደሚጠመቁ ይናገራሉ ፤ ይኸውም ቀን በዓለ ጥምቀት የሚከበርበት ነው ። ሆኖም ይህ አነጋገራቸው ፍጹም ስህተት የመላበት ነው ፤ በሃይማኖት ጸሎታቸውና በምዕላዳቸው ተለይቶ የተደነገገው ጥምቀተ ክርስትና የሚፈጸመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ሆኖም ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ይጠመቃሉ(ክርስትና ይነሣሉ)የሚለው ስህተት የመጣው የውጭ ሀገር ተመልካቾች የሆኑት ታሪክ ጸሐፊዎች በተቀደሰው በዮርዳኖስ ውሀ ምሳሌ የተባረከውን ውሀ ኢትዮጵያውያን ቀሳውስት ሕዝቡን ሲረጩ ፤ ሕዝቡም በባሕረ ጥምቀቱ ሲዋኝ ስላዩ—ነው ። ለምሳሌ እኛ ሩሲያውያን አንድ ልማድ አለን በዮርዳኖስ ውሀ ምሳሌ የተቀደሰውን ውሀ እንረጫለን ፤ የቻለም በዮርዳኖስ ውሀ ይጠመቃል (ይዋኛል) እኔ እራሴ ምስክር ነኝ ኢትዮጵያ በነበርኩበት ጊዜ በዓለ ጥምቀትን አብሬ አክብሬአለሁ ኢትዮጵያዊው ቄስ ሦስት ጊዜ ውሀውን በራሴ ላይ አፈሰሰብኝ ሥርዓተ ጥምቀት (ክርስትና ) ተፈጸመለት ብሎ ያሰበ ማንም ኢትዮጵያዊ አልነበረም» በማለት በኢትዮጵያ ጥምቀት የማይመለስ የማይከለስ መሆኑን «ከእንጦጦ እስከ ባሮ ወንዝ» በሚለው መጽሐፉ ከላይ የተጠቀሰውን እውነተኛ ማስረጃ ጽፎት ይገኛል ።

ይህ ሩሲያዊ የጦር መኰንን ከንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ሆኖ በደቡብ ኢትዮጵያ እስከ ኬንያ ወሰን እስከ ሩዶልፍ ሃይቅ ድረስ ተጉዞአል ። በአገራችን ያየውንና የሰማውን ሁሉ «ከዳግማዊ ምኒልክ ወታደሮች ጋር» በሚል አርእስት ያልጻፈው አልነበረም



# የመጀመሪያው ተአምር በሠርግ ቤት

ከቄስ መከብብ አጥናው

«ቤተ ሰብ አንድ ትንሽ መንግሥት ነው ። በዓለም የታወቀ ምንም ዓይነት ታላቅ መንግሥት ይኑር ያ መንግሥት የብዙ ቤተሰብ ድምር ነው» የአብዛኛው ቤተሰብ መሠረቱ ጋብቻ መሆኑ የማያከራክር ሐቅ ነው ።

ማናቸውም መንግሥት የሚመራበት የራሱ ሕግና ሥርዓት እንደሚያስፈልገው በሕጋዊ ጋብቻ የሚመሠረት ቤተሰብም እንደዚሁ የራሱ አቋም የሚታወቅበት መለኮታዊ ሕግና ሥርዓት አለው ። ይህም ሕግ ከመጀመሪያው ሰው ፍጥረት ጀምሮ የዘመናት እርዝመት ሳይሽረው ቀዋሚ ሆኖ የነበረና ያለ የሚኖርም ነው።ለዚህም ማስረጃ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ አይገባም የምትረዳው የኑሮ ጓደኛ እንፍጠርለት ። - - - ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፥ ሚስቱንም ይከተላል ፥ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ ። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይገባም» የተሰኙትን ቅዱሳት ቃላት መመልከቱ ይበቃል ።

በሌላም በኩል ለሰው ልጆች ሁሉ ደህንነት ሕይወቱን መሥዋዕት ለማድረግ ወደ ዚህ ዓለም የመጣው ክርስቶስ የመጀመሪያው ተአምር ብሠርግ ቤት ማድረጉ የጋብቻን ቅዱስነት በግልጥ የሚመሰክር ነው ። አወ በገሊላ አውራጃ ቃና ተብላ በምትጠራው ቀበሌ ሠርግ ነበር ። በዚያም ብሠርግ ቤት ለመገኘት ክርስቶስ ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተጠርቶ ነበር ።

ታዲያ በዚያ ሠርግ ቤት የተደቀነው አጋጣሚ ችግር ለተጋባዦች የተዘጋጀው የወይን ጠጅ በድንገት ማልቁ ነበር ። ይህን ችግር ለማስወገድ በእመቤታችን ቅ/ ድንግል ማርያም ጥያቄ መሠረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስድስት የደንጊያ ጋኖች ብውሃ እንዲሞሉ አዘዘ። ይህንም ውሀ ወደወይን ጠጅ እንዲለወጥ አደረገው ። ይህም የተአምራቱ ሁሉ መጀመሪያው ክፍል እንደ ነበር ወንጌላዊው ዮሐንስ ጽፎአል። (ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፩)

ከዚህም የምንማረው ብዙ ቁም ነገር አለ ። በመጀመሪያ ዕድለኛው ሙሽራ (ዶኪማስ) ይህን አጋጣሚ ለማግኘት የበቃው እንዴት ነው ? ብለን እንጠይቅ ። መልሱም በአጭሩ ክርስቶስን ወደ ሠርጉ ቤት በመጥራቱ መሆኑን እንገነዘባለን ። እንግዲያውስ ለማናቸውም የጋብቻ መሥራች የሚያስፈልገው ዋና ነገር ለሠርግ ድግስ ብዙ ሀብት በማባከንና የዕድምተኞችን ብዛት ከፍ በማድረግ ተከታዮችን ከማግበስበሱ ላይ አይደለም ። በዚያ ሠርግ ቤት ከተጠሩት ዕድምተኞች ጋር ክርስቶስ እንዲኖርበት ያስፈልጋል ማለትም የክርስቶስን ቅዱስ ስም በጸሎት መጥራት ያስፈልጋል ። ይህም ከሆነ በቃና ዘገሊላው ሠርግ ቤት ውሀው ወደ ወይን ጠጅነት ከተለወጠበት ተአምር የበለጠ ድንቅ ነገርን ሁሉ በተለያየ ሁኔታ ማየት ይቻላል ።

ክርስቶስ ውሀውን ወደ ወይን ጠጅነት መለወጥ ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ሕይወት የመለወጥ ኃይልና ሥልጣን አለው ፡ በርሱ ስም የተመሠረተም ጋብቻ አዲስ ፍቅርና ሰላም የሠፈነበት በበረከትም የተሞላ ይሆናል ። እንግዲያውስ የሠርገኞችና የዕድምተኞች ብዛት የሚያስከትለው ነገር ቢኖር ኪሣራ ብቻ መሆኑ ታውቆ ኪሣራን በበረከት

ለመተካት የክርስቶስን ቅዱስ ስም በጸሎት መጥራት የክርስቲያን ሁሉ ተቀዳሚ ዓላማ መሆኑ መታወቅ አለበት ። በየዓመቱ ይህኑ የክርስቶስ ተአምር ለመመሪያ ጊዜ የታየበትን የቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ታሪክ በማስታወስ በዓሉን የምናከብርበትም ዋናው ምክንያት ይኸው ነው ።

ነገር ግን የአንዳንድ ሰዎች አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ መሠረተ ቢስ ዝንባሌ አለው። ይኸውም ክርስቶስ ውሀውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ መጠጥ ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጣል በማለት ተሳሥተው ለማሳሳት ይሞክራሉ ። ይህም ሊበሉት የፈለጉትን እሞራ ጅግራ ነው ይሉታል እንደሚባለው መሆኑ ነው ። እንግዲየውስ «መንፈስ ይምላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» የሚለውን ቅዱስ ትእዛዝ ማስታወስ ይገባል ።

ሌላው አሳዛኝ ነገር መላው ኅብረተሰባችን ስለጋብቻ አፈጻጸም ባለው የተለያየ አቅዋም ዘላቂነት የሌለውን ጊዜያዊ ደስታ ለመሸመት ሲባል የማጫው ጥሎሽ ብዛት የድግሱ ጋጋታ (ወዘተ) በምጣኔ ሀብት በኩል የብዙዎችን ግለሰቦች የኑሮ አቋም ከማቃወስ ደረጃ ደርሶአል ። ይህንም ሁሉ በልዩ ልዩ ባህላዊ ተጽዕኖ ለይሉኝታ ጭምር የሚፈጽም እንጂ በአምላካዊ ትእዛዝ የተመሠረተ አለመሆኑ መታወቅ አለበት ።

ለዚህም በአንድ ወጣት ላይ የደረሰውን አንድ አጭር ታሪክ ማስታወስ ይበቃል ። ይኸውም የኑሮ ጓደኛ ለማግኘት ፈልጎ የጥሎሽና የድግሱ ወጭ ግራ አጋብቶት ችግሩን ለአንድ አዛውንት ያዋያቸዋል ። አዛውንቱም የችግሩን ብዛት ከተመለከቱ በኋላ «ምን አለው ብለህ ነው ? ለሠርጉ ድግስ በቀላሉ ሁለት ሠንጋ ብትገዛ አንዱ ለወጥ አንዱ ለቁርጥ ይበቃል» አሉት ይባላል ። እንዲህ ዓይነቱ ምክር አዲስ ኑሮ መሥራችን ያጽናናል ከተባለ አንባቢው ይፍረደው በበኩሌ ግን የብዙ ሕዝብ ቤተሰባዊ አቋም ቀርጾ ሊገጥም የቻለ በዚህ ዓይነቱ የግብዞች ምክር መሆኑ ይታየኛል ። ይህም በፍጥነት መታረም ያለበት ሥርዓት ነው ። የቤተ ሰባዊ አቋም በኢኮኖሚ መቃወስ ከግለሰብ ደረጃ አልፎ መንግሥታዊ አቋምንም የሚነካ ሊሆን ይችላልና ነው ። አሁንም እንኳ ለመንግሥት ራስ ምታት ሆኖ የሚገኘው ዝሙት አዳሪነት ራሱ የዚሁ የጋብቻ ቀውስ ውጤት መሆኑ አያከራክርም እያንዳንዱ ቤተ ሰብ ለድንቁርና ለበሽታና ለኑሮ ችግር መጋለጡ በሚጀምርበት ጊዜ ኅብረተሰብ የሚያጥለቀልቅ ይሆናል ። ይህ ሲሆን ደስ የሚላቸው ወገኖች ቢኖር «የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ብልህ ያለቅሳል» እንዲሉ የዕለቱን እንጂ የዘለቄታውን ኑሮ አርቆ መመልከት የጎደላቸው ናቸው ። ለዚህም ሁሉ ሌላ መፍትሔ (አማራጭ) የለውም ። በየአንዳንዱ ግለሰብ ላይ የወደቀውን ችግር መፍታት የሚችል በቅዱስ ጋብቻ የተመሠረተ የጋራ ጥረት ካለፈው ታሪክ መማር ይቻላል ። ከዚህም ሁሉ ጋር የክርስቶስ ጸጋና በረከት አስፈላጊ ነው ።

እርሱ በበረከት ላይ በረከትን የሚሰጥ የፍቅርና የሰላም ባለቤት ነውና ስለቅዱስ ጋብቻ ሰፋ ያለውን መንፈሳዊ ትምህርት አዘል መልእክት በሚከተለው ዝግጅት መመልከት ይቻላል ።



## መንፈሳዊ ደስታ በቅዱስ ጋብቻ

ጋብቻ ለሰው ልጅ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ፍጹም ደስታ ነው ። ጋብቻም ሰው ሠራሽ ተለዋጭ ፍልስፍና ያይደለ እግዚአብሔር የአዘዘው ትእዛዝ (ሕግ) በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ከምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን አንደኛው ክፍል በተቀደሰ የተክሊል ጋብቻ የሚፈጽመው መሆኑን መዝግባ ተከታዮቿ እንዲጠቀሙበት አድርጋለች ። ይህ ምሥጢር ድንቅ ነው ይህንንም ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርጌ እናገራለሁ። ይህች ጋብቻ በሕግ የከበረች ናትና ኤፌ ፭ ፴፪ የሕይወታችን መሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ዓለም እየተዘዋወረ ሲያስትምር ጋብቻ ቅዱስና አስፈላጊ መሆኑን በቃላት ብቻ ሳይሆን በግብር ክቡርነቱን በማረጋገጥ ሠርግ ቤት እንደተጠራ ጥሪውን አክብሮ እንደሄደና ክብሩን እንደገለጠ የመጀመሪያውን መክስተ ተአምራት በዚያው ሠርግ ቤት እንደፈጸመ ተጽፏል ፤ ዮሐ ፪ ፩—፲፫ በሌላ በኩል ደግሞ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርበው የእነሱን ጽድቅ በመግለጽ እኛ ፈሪሳውያን ብዙ እንጾማለን ደቀመዛሙርትህ ለምን አይጾሙም ብለው ለጠየቁት ሲመልስ ሚዜዎች ከሙሽራው ጋር እያሉ መጾም የማይገባ መሆኑን በመግለጽ የጋብቻን ክቡርነት በምሳሌ አስረድቷል ማቴ ፱ ፤ ፲፬—፲፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ለሰው ልጆች መሥዋዕት አድርጎ ሲሰጥ ንጉሥ ለሠርግ እንደ አዘጋጀው ፊሪዳ በምሳሌነት እንደ ቀረበና ዳግመኛ በዓለም ላይ ሊፈርድ በክብር በግርማ መለኮት አመጣጡን ሙሽራውን በሚጠብቁ ደናግል ጠባባት በማገናዘብ ሙሽራው ፤ እራሱ ደናግል ጠበባት መንግሥተ ሰማይ መሆኑን የጋብቻን ክቡርነት በተጨባጭና ጉልህ በሆነ ማስረጃ በምሳሌና ያለ ምሳሌ የተገለጸው በቂ ማስረጃ ነው ። ማቴ ፳፪፤ ፩—፲፬ ፤ ፳፭ ፩—፲፬ ፤

ጋብቻ ለምን አስፈለገ ፤ ሀ/ ጋብቻ የአስፈለገው አዳምና ሔዋን ከመበደላቸው አስቀድሞ ፤ ሰው ብቻውን ሊኖር አግባብ አይደለም የምትረዳው ሴት እንፍጠርለት ተብሎ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ በመሆኑ ፤ በጋብቻ የተሳሰሩት ሁለቱ ባልና ሚስት አንዱ ቢደክም አንዱ ሊያጽናና ፤ አንዱ ቢያዝን ቢተክዝ ፤ ቢታመም የማይችለው ችግር ቢገጥመው አንዱ ሊያጽናናው ሊያስታምመው የችግሩ ተካፋይ ለመሆንና ተረዳድተው ለመኖር ፤ ለ/ ሰው በጥንተ ተፈጥሮ ከማንኛውም ፍጥረት የላቀ በአእምሮ የመጠቀ የእግዚአብሔር መልክ የተሳለበት ሲሆን እንደ ሌሎች እንስሳትና አራዊት በየተገኘበት የዝሙት ተግባር እንዳይፈጽም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ፤ መኝታውም ንጹሕ ነው ፤ ዕብ ፲፫—፬—፭ በአለው ቃል መሠረት ባል በሚስቱ ሚስት በባሏ ጸንተው ተወስነው እንዲኖሩ ፤ ሐ/ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት ፤ ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል «መዝ ፻፳፯-፻፳፰ ፤ ፫-፭ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ለማግኘት «ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉ» ያለውን በመፈጸም ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ የተባረኩ የተቀደሱ በልዑል እግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ የሚሄዱ ህጻናትን ለመተካት ወይም እንዲወለዱ ለማድረግ ነው ።

ሁለቱ የሚጋቡ ለመጋባት እቅድ ያዘጋጁ ወጣቶች ከመጋባታቸው በፊት ዘላቂ ደስታን ለማግኘት ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄ ፤ ፩ ሁለቱ ጾታ ዎች በዚህች ጥላ ዓለም ለሚቆዩባት ጊዜ ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስማያዊት እንዲያበቃቸውና «ያለኔ ምንም ማድረግ አይቻላችሁም» በአለው አምላካዊ ቃል መሠረት እሱም መሰሉን እሷም መሰሏን እንዲያጋጥማቸው የዘለዓለም ደስታ እንዳይለያቸው እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ምኞትን ሐሳብን መግለጽ ነው ። መዝ ፴፮ ፬—፮ ይህንንም የመጀመሪያው ሰው አዳም

የፈጸመው ስለሆነ አባታችን አዳም የፍጥረታት ሁሉ ገዥነት ሥልጣን በተሰጠው ጊዜ ፍጥረታት በሙሉ በየነገዳቸው ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ እርሱ ቀርበው ስም ስም እንዲያወጣላቸው ሲመጡ በማየቱ ብቻኛ በመሆኑ ጓደኛ የማግኘት ፍላጎት ተፈጠረበት ማለት ሚስት ፈለገ እግዚአብሔርም እንደ ፍላጎቱ የአማረች ውብ ቆንጆ ማለት መሰሉን አዘጋጀለት ዘፍ ፪ ፳፩—፳፭ ።

፱- ወጣቷም ሆነች ወጣቱ ከተጋቡ በኋላ ልዩ ጸጸት እንዳያድርባቸው በመጀመሪያ መመራረጥ ፤ መፈላለግ ፤ መተዋወቅ ፤ መወሰንና ከዚያም ለእናት አባት ማሳወቅ የእነሱን ፈቃደኛ መሆን መጠበቅ ያስፈልጋል ። የይስሐቅና የርብቃ እንዲሁም የያዕቆና የራሔል የጋብቻ አፈጻጸም እንዲህ ነበርና ዘፍ ፳፬ ፩-፷፯ ፤ ፳፱ ፩—፴ ፤

፲— ምንም እንኳን መልክ ውበት የጢት ጤዛ መሆኑን ብንገነዘብም ጤዛም ቢሆን እስከ አለበት ጊዜ ድረስ እንደ አለ ስለሚቆጠር ወጣቷም ሆነች ወጣቱ በመልክ ፤ በዕድሜ ፤ በእውቀት ፤ የተቀራረቡና የተመሳሰሉ መሆን አለባቸው ከእሱ ዘንድ የሌለውን ከእሷ ዘንድ፣ከእሷ ዘንድ የሌለውን ከእሱ ዘንድ መፈለግ ከተጋቡ በኋላ ጸጸትን አሳድሮ ወይኔ እንዲህ የአለ እውቀት መልክ፤ ልጅነት እያለኝ ከዚህ አላዋቂ ፤ መልከ ጥፉ ፤ ሽማግሌ ወይም አሮጊት ጋር መኖሬ በማለት እሷም ሆነች እሱ ወደ መሰላቸው በመሄድ«አታመንዝር» ያለውን ሕግ በማፍረስ ዝሙት በመፈጸም ምድራዊውንና ሰማያዊውን ቤታቸውን ለማፍረስ ይገደዳሉ የእድሜውም ገደብ ወንድ ከ፲፰ ዓመት በላይ ሲሆን ሴቷ ደግሞ ከ፲፭ ዓመት በላይ መሆን አለባቸው በዚህ ክልል ዕድሜ ውስጥ የአሉ ሁለት ወጣቶች በውዴታ የሰጡት ቃላቸው የጸና ይሆናል ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ።

፲፩- የጋብቻ አፈጻጸም በሀብት በንብረት ፤ በገንዘብ ተገዥነት እንዳይሆን ፤ ከሆነ ግን ግዕዛን እእምሮ የአለውን ሰው ማግባቱ ቀርቶ ግዕዛን አእምሮ የሌለውን ግዑዝ ነገር ማግባት ስለሆነ የዚህ ዓለም ሀብት አለ ሲሉ እንደ ጥላ ፀሐይን አይቶ ውልብ ብሎ ሲጠፋ ወይም እንደዳልነበረ ሲሆን ፤ መጀመሪያውንም የአገቡት ግዕዛን የሌለውን ሀብት ነበርና ወዲያው ይፋቱና ያንኑ የሚንገበገቡለትን ገንዘብ ፍለጋ ውዳቂ እንዳዩ ሲስገበገቡ አንድ ቀን ደስታን ሳያዩ ወደ መጡበት ባዶ እጃቸውን ተመልሰው ይሄዳሉ።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ጢሞቲዎስ የዚህን ዓለም ሀብት እንዳይመኝ ሲጽፍለት «ወደ ዓለም ምንም አላመጣንም አንዳችም ልንወስድ አይቻለንምና ምግብና ልብስ ከኖረን እርሱ ይበቃናል» ዳሩ ግን ባለጸጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያስጥም በሚያሰንፍና በሚጎዳም በብዙ ምኞት በፈተና በወጥመድ ይወድቃሉ ገንዘብ መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶች ይህንን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ እራሳቸውን ጐዱ ፩ኛ ጢሞ ፮ ፯-፲፩ ስለዚህ የሚጋቡ ወጣቶች በመንፈሳዊ ሕይወት አንድ መሆን በጠባይ መግባባት ነው እንጂ የሚያስፈልገው የዚህ ዓለም ሀብት እነርሱ ሠርተው የሚያገኙት ነው ።

፲፪- የሰው ዘመኑ እንደጥላ ነው እንደሜዳም አበባ ፈጥኖ ያብባል ፈጥኖም ይረግፋል ። እንደተባለው ሰው በዚህ ዓለም የሚኖረው እንደ ጥላና እንደ አበባ እንደ ጤዛም ነው አበባውም ጤዛውም ጥላውም እንደሚያልፍ እንደሚረግፍ የሰው ልጅ በዓለም ላይ ለተወሰነ ጊዜ ይኖራል ለባለተራ አስረክቦ ይሄዳል ይህ ያልገባቸው አንዳንድ ወጣቶች ዘለዓለም እንደነበሩ ሆነው መኖር የአለ እየመሰላቸው እራሳቸውን በራሳቸው በማታለል የማይተካው ሰውነታቸው ማለት ውበት ፤ ደም ግባት ጊዜውን እየቆጠረ ሥፍራውን እየለቀቀ ሲሄድ ቆይ ነገ ከዚያም መከራ በማለት የተፈላጊነት ጊዜዋ ወይም ጊዜው ሲያከትም ፈላጊ በማጣት ዋግ እንደ መታው አበባ ያለ ፍሬ ከመቅረታቸው በላይ የፈለጉትን ሳያገኙ የዘለዓለም ጸጸት በማትረፍ የሚፈልግ ሁሉ አበባው ሳይረግፍ



ፍሬ ተክቶ በምግባረ ሠናይ ብልጽግና ክርስቶስ በሰማያዊ አዳራሽ ለሚያደርግላት የመልስ ጥሪ ዝግጁ መሆን አለበት ተፈላጊውና ውድ ስጦታ የሆነው ጋብቻ ይህ ነውና ወጣቶቻችን መትጋትና መቅናት ያለባቸው ለዚህ ነው ።

፲፫- ሁለቱ ለመጋባት የወሰኑ ወጣቶች የተክሊሉ ጋብቻ እስከ ተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ንጽሕናቸውን ቅድስናቸውን በመጠበቅ ከሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መከልከል ግዴታቸው ከመሆኑም በላይ ሁለቱም ክፍሎች የጋብቻቸው ዕለት የሚጠበቅባቸውን መረካከብ አለባቸው እሷም የእኔው ናት እሱም የእኔው ነው በማለት በቅድሚያ የሚፈጸመው ድርጊት የሰባራ ብርሌ ምሳሌነትን ያመለክታል ።

ጋብቻው በተክሊል ከተፈጸመ በኋላ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አካል አይባሉም ። «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ዘፍ ፪፳፬ ማቴ ፲፱፭ ባልና ሚስት አንድ አካል ከሆኑበት ቀን ጀምሮ ሞት ከአልሆነ በቀር መለያየት አይፈቀድላቸውም «እግዚአብሔር አንድ የአደረገውን ሰው ሊለይ አይችልም ማር ፱-፱ እንዲሁም «ማንም የልጅ ነት ሚስቱን አይፍታ ትንቢተ ሚልክ ፪-፲፬-፲፮ ወንድ ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድረግ ይገባዋል ፤ ሴትም ለባሏ የሚገባውን ማድረግ ይገባታል ሴት ባሏ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጂ በባሏ ላይ የሌላ ትእዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራሷ ላይ ሥልጣን የላትም በእርሷ ላይ የሚያዘው ሥልጣን ያለው ባሏ ብቻ ነው እንዲሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላይቱ ታዛዥ ሊሆን የሌላይቱን ፈቃድ ሊፈጽም በራሱ ላይ የማዘዝ ሥልጣን የለውም በእሱ ላይ ሥልጣን ያላት የምታዝበት ሚስቱ ናት ፩ኛ ቆሮ ፯፭-፱ ሚስት የሥጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ባሏን በመውደድ እግዚአብሔርንና ሰውን በሚገባ በማስደሰት በመንፈሳዊ ኃይል በመመራት ፈቃደ ነፍስን በመሥራት ብትኖር ከእግዚአብሔር ዘንድ የማያልፍ ዋጋ ይጠብቃታል ወንድም የዚህ ዓለም ሀብት ንብረትና ክብር ብቻ ፈላጊ ሳይሆን የልጅነት ሚስቱን የይንቅ እንደ አይኑ ብሌን በመጠበቅ በክርስቲያናዊ ሕይወት በጽናት ርስት መንግሥተ ሰማይን በማዘጋጀት ሲሆን ፤ በክርስቲያናዊ ሕይወት የቅዱስ ጋብቻ ወጤት ይህ ነው ።

እማረ ካሳዬ

# "የእግዚአብሔር መኖር በሥነ ፍጥረት ይታወቃል"

ከተሰፉ ጥሩነህ

«ከዚህ በፊት የእግዚአብሔርን መኖር ይጠራጠሩ የነበሩት እንደ አዋቂዎች ይገመቱ የነበሩት ሰዎች ናቸው ። በእግዚአብሔር ያምኑ የነበሩት ብዙ ዕውቀት ያልነበራቸው ተራ ሰዎች ነበሩ ፤ አሁን ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው የእግዚአብሔርን መኖር ሲያረጋግጡ ጥልቅ ዕወቀት የሚያንሳቸው ደግሞ የእግዚአብሔርን መኖር መጠራጠር ጀምረዋል ።»

ይህንን የተናገረው ገተ የተባለው የጀርመን ባለ ቅኔ ነው ፤ አሁን ባለንበት ዘመን ስለእግዚአብሔር መኖር የሚጠራጠሩት ለምርምር የሚያበቃ ዕውቀት የሌላቸው አንዳንድ ሰዎች ብቻ ናቸው። የእግዚአብሔርን መኖር በቀላሉ ለማረጋገጥ ስለማይቻል እራስን በመጠየቅ መመራመር ያስፈልጋል ። የሰው ተፈጥሮ እራሱ የእግዚአብሕር ህልውና መግለጫ ነው ፤ ሰው በሚሠራው ሥራ የእግዚአብሔርን ህልውና ይገልጻል ። የታረዙትን ማልበስ ፤ የተራቡትን ማብላት ፤ ከጭቆና ቀንበር ለመላቀቅ የሚታገሉትን መርዳት እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው በጎ ሥራዎች ስለሆኑ የህልውናው መግለጫዎች ናቸው ፤ ምክንያቱም የመልካም ሥራዎች ሁሉ ምንጭ እራሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው ።

የእግዚአብሔር መኖር የሚረጋገጠው በመመራመር ብቻ ሳይሆን በእምነትም ጭምር ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን «እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥና የማይታየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው ።»

የሰው ልጅ ከብዙ ጊዜ ምርመራና ጥረት በኋላ ልዩ ልዩ አስደናቂ ሥራዎችን ሠርቷል ፤ በመሬት ላይ የሚሽከረከሩ መኪናዎችን፣በሰማይ የሚበሩ አእሮፕላኖችን፣በባሕር ላይ የሚንሳፈፉ መርከቦችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ጥበባትን በማስገኘቱ የሰው ልጅ አስደናቂ ሥራዎች መሥራቱን እንረዳለን ። ለአብዛኞቻችን ተአምር መስለው የሚታዩትን ሁሉ የሰው ልጅ ማስገኘቱ የእግዚአብሔርን ህልውና የሚገልጽ ነው ፤ እግዚአብሔር የጥበብ ሁሉ ምንጭ ስለሆነ ጥበባቱን ሁሉ ለሰው ልጆች አድሏቸዋል ። ስለዚህ በሰው ልጆች ጥበብ የእግዚአብሔር መኖር ይታወቃል ፤

የእግዚአብሔርን መኖር የሚጠራጠሩና ለሌላም የሚያስተምሩ ሁሉ በቂ ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች ናቸው ፍራንሲስ ቤክን የተባለው የሃይማኖት መምህር «ጥቂት ፍልስፍና ሰውን ከክህደት ያደርሰዋል» ፤ ነገር ግን ጠለቅ ያለ ፍልስፍና ና እውቀት ወደእግዚአብሔር ያደርሰዋል ሲል ተናግሯል ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሰው እግዚአብሔር ፈጣሪውን ለማየት ከፈለገ አያጣውም፡ ግን አስቀድሞ መልካም ሥራ ሠርቶ መገኘት አለበት ። መልካም ሥራ ሠርቶ ከተገኘ ሰው እግዚአብሔርን በተለያዩ መንገዶች ሊያገኘው ይችላል ። ለምሳሌ የራዲዮ ድምፅና የትንደኛድ ድምፅ እንደምንሰማ ሁሉ እግዚአብሔርንም በሚያሰማን ድምፅ አማካይነት መኖሩን ለማረጋገጥ እንችላለን ።

እግዚአብሔርን በርቀቱ ማየት ግን እንደማይቻል ቅዱሳን ነቢያት በየጊዜው ተናግረዋል ፡ እራሱም እግዚአብሔር ሰዎች በርቀቱ ሊያዩት እንደማይቻላቸው ሲና



ገር እንዲህ ብሏል ፤ «ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም።» ሙሴም የእግዚአብሔርን መኖር ያወቀው በእሳት ነበልባል መልከፍና ባሰማው ድምጽ ብቻ ነበር ፤ እንጂ በዓይኑ ሊያየው አልቻለም ።

እግዚአብሔር በደነገገላቸው ሥነ ሥርዓት እንስሳት ሰዎች ዕጸዋት በጠቅላላው በዓለም የሚገኙት ነገሮች ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ አላቸው ፤ ተወልደው አድገው ከጥቂት ጊዜ በኋላ አርጅተው እንዳልነበሩ ይሆናሉ ፤ እግዚአብሔር ግን መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ ነው ፤ በዘለዓለማዊነቱ ሕልውናውን ልንረዳ እንችላለን ። ቅዱስ ዳዊት የእግዚአብሔር መኖር የሚታወቀው በዘለዓለማዊነቱ መሆኑን ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፤ «ሁሉ ነገር እንደልብስ ያረጃል ፤ አንተ ግን መቸም መች ያው ነህ፤ ዓመታቶችህም ከቶ አያልቁም ። »

እግዚአብሔርን በጥሞና የፈለገና መኖሩን ለማረጋገጥ የተመራመረ ሰው ሁሉ የሰው ልጆች ባስገኙት ጥበብ ፤ በመልካም ሥራቸው ፤ እንዲሁም በተፈጥሮ ሕግ ውስጥ ሊያየውና መኖሩን ሊያረጋግጥ ይችላል ፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔርን እንደቁሳቁስ በሚያኅላ መነጽር አማካይነት ለማየት አይቻልም ፤ የሚያጕላውን መነጽር ሰው እንዲፈለስፍ ጥበቡን የገለጸለትን ተመራምሮ የሚፈለግ ግን እግዚአብሔር መሆኑን ስለሚያረጋግጥ የእግዚአ ብሔርን መኖር ሊረዳ ይችላል ።

# ምሥጢረ ንስሐ ፤

ምሥጢር የሚለው ቃል «ሚስቲርዮን» ከሚለው ግሪካዊ ቃል የተወረሰ ነው፣ትርጓሜውም የተዘጋ ፤ የተቆለፈ ወይም የተሠወረ እንደማለት ነው ፤ በእኛም አመለካከት ምሥጢር ሲባል ለማንም የሚነገር ሳይሆን ከልብ ለሚያምኑትና ለሚወዱት ጓደኛና ዘመድ የሚያካፍሉት ነው ። ንስሓ ማለት ደግሞ መጸጸትና ካደረጉት ስሕተት መመለስ ነው ።

እንደ ቤተክርስቲያናችን ሕግና ሥነ ሥርዓት የሚፈጸሙ ሰባት ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን አሉ ፤ እነዚህም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረቱ ሲሆኑ የሰውን ልጅ ለዘለዓለማዊ ድኅነት የሚያዘጋጁና የእግዚአብሔርም ጸጋ የሚሰጥባቸው ናቸው ። ምሥጢሩ ንስሓም ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መካከል አንዱ ነው ። ዐይን በሚታይና በጆሮ በሚሰማ ምሳሌ በዓይን የማይታየውንና በጆሮ የማይሰማውን ጸጋ እግዚአብሔር የሚያሰጥ በመሆኑ ምሥጢረ ንስሓ ለመባል በቅቷል ፤ ይህም ማለት ምእመናን ምንም እንኳን በጥምቀት ዳግመኛ ከክርስቶስ ቢወለዱም ከኃጢአት ነጻ ሁነው ለሁልጊዜ ለመኖር ስለማይችሉ በየጊዜው በንስሓ መታደስ ያስፈልጋቸዋል ።

የመጀመሪያው ሰው ባደረገው ጥፋት ተፈርዶበት ከገነት ከወጣ በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገባ ተስፋ የተሰጠው በንስሐመሆኑንቅዱሳትመጻሕፍትያስረዱናል ፈጣሪያቸውን በድለው በንስሐ የታደሱ ብዙዎች ናቸው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን በደለኛው በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ አስቦ ወደፊት ኃጢአት ላለመሥራት ቁርጥ ሐሳብ አድርጎ የሠራውንም በደል ሳይሠውር ከተናዘዘ ከኃጢአቱ በቀላሉ ሊነጻ ይችላል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ስለንስሓ ኃይል ሲገልጽ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች ፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች» ይላል ኢሳይያስ ፩ ፲፰

በሐዲስ ኪዳንም ስለ ንስሓ አስፈላጊነት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው መጥምቁ ዮሐንስ ነው ። ዮሐንስ መጥምቁ ፍሬቢስ ቅርንጫፎችን ለመቁረጥ ምሣር በዛፎች ላይ ተቃጥቷልና ከእንግዲህስ ወዲህ ለንስሐ የሚያበቃ ሥራ ሥሩ፣መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ በማስተማሩ በሐዲስ ኪዳን ዘመን የታወቀ ግምባር ቀደም የንስሐ መምህር ለመባል በቅቶአል ።

ዮሐንስ ክርስቶስን ከማጥመቁ አስቀድሞ የንስሐ ጥምቀት ሲያጠምቅ መቆየቱ ቢታወቅም ጥምቀቱ ሥርየተ ኃጢአት ያለውና ለመንግሥተ እግዚአብሔር ም የሚያበቃ አልነበረም ። ይህንንም «እኔ ለንስሐ በውሀ አጠምቃችኋለሁ፣ከእኔ ቀጥሎ የሚመጣው ግን ከእኔ በፊት የነበረ ሲሆን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል» ሲል ራሱ ገልጾታል ። ማቴ ፫ ፲፩ የቅዱስ ኪዳን ንስሐ መሠረትም በዚህ ጊዜ ተወጠነ ለማለት ይቻላል ።

ሳያውቁ በስሕተት እያወቁ በድፍረት ኃጢአት የሠሩ ሁሉ የሠሩትን ኃጢአት አስታውሰው ከተናዘዙ በኋላ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ይችሉ ዘንድ ይህ ምሥጢረ ንስሐ ተሠርቷል ፤ በእውነት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የተመለሱትን ከበደላቸው



ነጻ ይወጡ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልጋዮቹ ሥልጣንን እንዲሰጣቸው መጠን በሠሩዉ ኃጢአት ያዘነና የተጸጸተ ሰው ሁሉ የሠራውን ኃጢአት ሳይሠውርና ሳያፍር በካህኑ ፊት ቢናዘዝ ሥርየተ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚያገኝ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታምናለች ። ታስተምራለችም ።

ሆኖም የምሥጢረ ንስሐ አፈጻጸም በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የተለያየ ይዘታ እንዳለው መዘንጋት የለበትም ።

ለምሳሌ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቲንሣሒው ኃጢአቱን ለቄሱ የሚናዘዘው ፊት ለፊት ተገልጾ ሳይሆን በሥውር ነው ፤ ይህም ማለት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ ልዩ ክፍል ውስጥ ዘግቶ ይቀመጣል ፤ በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በእየተራ እየቀረበ ኃጢአቱን በመናዘዝ ንስሐውን ይቀበላል ።

ከዚህም ሌላ ይህ ዓይነት ሥርዓት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሐልዮን እንደተፈጸመ ኃጢአት በመቍጠር ንስሓ ይሰጣሉ ፤ ለዚህም መሠረት አድርገው የሚነሡበት ወደሌላይቱ ሴት ያየና የተመኛትም ከእርሷ ጋር አመንዝሯል የሚለውን ቃል ነው ፤ ማቴ ፭ ፳፯፤ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ቄሱና ተነሣሒው ፊት ለፊት እየተያዩ አስፈላጊውን የንስሐ ምሥጢር ይወያያሉ ማለት በደለኛው ኃጢአቱን ለቄሱ ይናዘዛል ፤ ቄሱም እንደ አስፈላጊነቱ እያየ ንስሐውን ለተናዛዡ ይሰጠዋል ፤ ስለ ሀልዮ ኃጢአት የተለያየ የንስሐ ጉዳዩ እንዲወድም ባታደርግም ቄሱ በሚያደርገው የዘወትር የንስሐ ጸሎት ሁሉ በሀልዮ የተሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር ይፍታ በማለት ስለሚናዘዙ የሀልዮን ኃጢአትም በቀላሉ እንደማትመለከተው ያስረዳል ። ሌሎቹ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ስለ ንስሐ የተለያየ አስተሳሰብ አላቸው ፤ አብዛኞቹ ፕሮቴስታንቶች ንስሐን እንደ ምሥጢር አድርገው አይቀበሉትም፤እንደ እነርሱ አስተሳሰብ የሠሩትን ኃጢአት ቢቻል በሕዝብ ፊት መናዘዝ መናገር እና አማኞች ስለ በደሉ እንዲጸልዩለት ማድረግ፤ካልተቻለውም ራሱ የተለየ ጊዜ ወስኖ ወደ እግዚአብሔር ይቅርታ መጠየቅ አለበት ይላሉ ፤ በ፲፯ ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተነሥቶ የነበረው ካልቪን ግን ንስሐ የጥምቀት መታሰቢያ ነው እንጅ ኃጢአትን አያስተሠርይም የሚል አስተሳሰብ ነበረው ።

የእኛ ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም የተለየ የንስሐ ሥርዓት ስላላት «ንስሐ የበደለውን እንዳልበደሉ፤ዘማዊውን እንደ ድንግል ታደርገዋለች » ብላ ያለ ጥርጥር ታስተምራለች ።
ይህንን ምሥጢር ለመፈጸም ለመጀመሪያ ጊዜ ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት ቢሆኑም ከእነርሱ ቀጥለው ለተነሡ ካህናትም ተሰጥቷቸዋል ።

ምሥጢረ ንስሐ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አራተኛውን ተራ ቍጥር የያዘ መሆኑ ቢታወቅም የሚፈጸመው ያው እንደተገለጸው በኤጲስ ቆጶሳትና በቀሳውስት አማካይነት መሆኑ የተረጋገጠ ነው ፤ ንስሐም የሚገባ ሰው በመሠረቱ አማኒ መሆን አለበት ፤ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ግን ንስሐ ሊቀበል አይችልም ።

ምሥጢረ ንስሐ ያለማቋረጥ እንዲሠሩበት ጌታችን ለሐዋርያት ሥልጣን ሲሰጥ «የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጣችኋለሁ ፣ በምድር ያሠራችሁት በሰማይም የታሠረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታ ችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ብሎ ተናግሯል (ማቴ ፲፰ ፲፰)

ማንም ሰው ለመዳን የሚችለው ከልቡ ተንኮልን ፤ ምቀኝነትን ፤ ጥላቻን ፤ ጸብን ክርክርን ፤ በደልንና የሚያስሉትን አስወግዶ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ የተመለሰ እንደሆንና በካህኑም አማካይነት በደሉን የተናዘዘ እንደሆነ ነው ፤ የተነገረው ሲናዘዝ ካህኑም የሚገባውን ጸሎት ያደርግለታል፤የበደላችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ ይቅር ይላችኋል፡ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ ይቅር አይ ላችሁም ፡ የሚል አምላካዊ ቃል ስላለ ቂም ይዞ ንስሐ መግባት ዋጋ የሌለው ከንቱ ድካም መሆኑን ካህኑ ለተነሣሂው ያስገነዝባል ። (ማቴ ፮ ፲፬)

እግዚአብሔር አምላካችን በንስሐ ወደ እርሱ የተመለሰውን ሁሉ በይቅርታ እንደሚቀበለው «ወደ እኔ የመጣውን ወደ ውጭ አላወጣውም» ሲል ተናግሯል በዚህ መሠረት ሦስት ጊዜ መላልሶ የካደው ጴጥሮስ ንስሐ ቢገባ ይቅርታ ተደርጐለታል ፤ እንዲሁም በዝሙት ምክንያት ተይዛ በደንጊያ ተወግራ እንድትሞት የተፈረደባትም ሴት ይቀር ብሏታል (ዮሐ ፰ ፲፩) እርሱም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለሰቀሉት ፤ ዐመፀኞችና በደለኞች ይቅርታ ያገኙ ዘንድ «አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢ የአምሩ ይገብሩ » ባለማወቅ ነውና ያደረጉት ይቅር በላቸው ሲል ወደ ባሕርይ አባቱ ጸልዮላቸዋል ።

ለማናቸውም ኃጢአት ይቅርታ ስላለው ቀሳውስት የሕይወት ድልድይ ሁነው ሰውንና እግዚአብሔርን በመንፈሳዊ አገልግሎት የሚያገናኙ ስለሆኑ ምእመናን ይህን አገልግሎት በቀላሉ ሊመለከቱ አይገባቸውም ። በየጊዜው ሊጠቀሙበት ይገባል ። ንስሐ ለሰው ልጅ ከፍ ያለ ጥቅምን ያበረክታል ፤ ለምሳሌ ውሀ ያደፈውን ልብስና የቆሸሸውን የሰው አካል ንጹሕ እንደሚያደርግና እንደሚያበረታ ንስሐም በኃጢአት የተጎሳቆለውንና ያረጀውን ሰውነት ያድሰዋል ፤ ንጹሕም ያደርገዋል ።

በንስሐ መመለስ ሁለተኛ እንደመወለድ ወይም በእየጊዜው እንደመታደስ ነው ፤ ማንም ሰው በእየጊዜው ኃጢአት ይሠራል ግን ኃጢአቱን እየተናዘዘ ሊታደስ ይችላል እየበደለ ባይመለስና በበደል ላይም በደልን እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ ግን በእርጅና ላይ እርጅናን በበሽታ ላይ በሽታን እያከለ ይሄዳል ።

ንስሐ የሚገባ ሰው ሁል ጊዜ የሐኪምን እርዳታ ከመጠየቁ የተነሣ በጤና የሚኖር ሰውን ይመስላል ።

ስለዚህ ማነኛውም በደለኛ የሆነ ሰው ሁሉ ፤ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ በቀሳውስትና በመምህራን ቃል ይጋበዛል ፤ ይህንን ጥሪ ተቀብሎ ራሱን በንስሐ የማይመረምር ክርስቲያን ራሱን ለኵነኔ ያደርሳል ። «ራስህን ለካህን አሳይ» እንደተባለው ሁሉም ክርስቲያን ባለፈው በደሉ በመጸጸት ንስሐውን በመናዘዝ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳለበት ሊገነዘበው ይገባል ፤ ቤተክርስቲያን ስለምሥጢረ ንስሐ የምታስተላልፈው መልእክት ይህ ነው ። ኃጢአተኛውን ወደ ንስሐ መመለስም የዘወትር ተግባሯ ነው ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ ፡



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ደመወዛቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ስለ መፍቀዳቸው ለቀረበላቸው ጋዜጣዊ ጥያቄ የሰጡት መልስ

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፫ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እንደቀድሞቹ የኢትዮጵያ ፓትርያርኮች በየወሩ ሊከፈላቸው የሚገባው ደመወዛቸው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ስለፈቀዱ ይህንኑ ምክንያት በማድረግ ጥር ፬ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ረቡዕ በመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤታቸው ተገኝተው ስለ ዚሁ ጉዳይ ለቀረበላቸው ጋዜጣዊ ጥያቄ መ ል ስ ሰጥተዋል ጥያቄውና መልሱም ከዚህ ቀጥሎ የሰፈረው ነው ።

ጥያቄ፤ ብጹዕ ወቅዱስ አባታችን በየወሩ ሊከፈልዎት የሚገባው ደመወዝ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል መፍቀድዎና ጉዳዩ በመንግሥት ደረጃ የታወቀ መሆኑ በአካባቢያችን ይወራል ነገሩ ምን ያህል እውነትነት አለው ?

መልስ፣ ነገሩ እውነት ነው የሚወራም በእውነት እንጂ በሐሰት አይደለም፣ መቸም ቢሆን የደመወዝ ልማድ የለኝም በወላይታ አውራጃ ለ፴፰ ዓመታት ያህል ሐዋርያዊ አገልግሎቴን በእግዚአብሔር ቸርነት ስፈጽም በማንቲም የሚቆጠር ደመወዝ አላውቅም ነበር ። አሁንም ቢሆን ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለዚሁ ታላቅ ክብር ብበቃ ወገኖቼ ካህናት እየተራቡ የእነሱ ኑሮ ሳይስተካከል የእኔ ደመወዝተኛ መሆን ፍትሕ ማጓደል ስለሆነ ደመወዜ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ወስኛለው ። (ፈቅጃለሁ)

ጥያቄ ፣ ብጹዕ ወቅዱስ በፓትርያርክነትዎ በዓለ ሢመት ታትሞ በወጣው መጽሔት የቅዱስነትዎ የሕይወት ታሪክ እንደተገለጸው የወላይታ አውራጃ ሐዋርያ በነበሩበት ጊዜ አትክልት በመትከልና ልዩ ልዩ ተግባረ ዕድ በመሥራት ይጠቀሙ እንደነበር ታትቷል ዛሬ ይህን ለመፈጸም ከማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል ለአባትነትዎ የተመደበው ደመወዝ ለሌላ አገልግሎት የሚውል ከሆነ «ነፍስ ያለ ሥጋ አትቆምም» ተብሏልና በቅዱስነትዎ ላይ ከፍተኛ ችግር አይደርስምን ?

መልስ ፣ በእርግጥ ነፍስ ያለ ሥጋ እንደማትቆም የተረጋገጠ ነው ስለሆነም እንደአባቶቼ እንደ ሐዋርያት በማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ ለዕለት ጉርሴና ለዓመት ልብሴ የሚበቃኝን እንዲሁም ለእንግዳ መቀበያና ለልዩ በረከት የሚሆነውን አመዛዝኖ መመደብ የአስተዳደሩ ክፍል ድርሻ ነው ፣ ይህም ለእኔ ተብሎ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ክብር መሆኑ መታወቅ አለበት ። በዚሁ መሠረት ይህን የመሰለው የተቀደሰ ሐሳብ በሥራ ላይ እንዲውል ከአስተዳደሩ ክፍል ባለሥልጣኖች ጋር በመነጋገር ተወስኖ ይሠራበታል ።

ጥያቄ ፡ ብፁዕ አባታችን የምዕመናኝ እረኛ (ጠባቂ) እንደመሆንዎ መጠን ለስብከትና ለበረከት ከስፍራ ወደ ስፍራ ሲዘዋወሩ የቅዱስነትዎን እጅ የሚመለከቱ ችግረኞች መኖራቸው አይቀርም ፡ እነዚህም ችግረኞች «ችግረኛን ሰው ሂደህ እሳት ሙቅ ልትጠግብ ትችላለህ ቢሉት ሊጠግብ አይችልም» ተብሎ እንደ ተጻፈው የማያቲም ድቃቂና የልብስ እላቂ ካልጣሉላቸው በደረቅ ቃል ብቻ ሊረኩ አይችሉም ፡ ሌላም ይህን የመሰለ ምግባር ሠናይ አለ በዚህ እረገድ ቅዱስነትዎ ደመወዝዎን በቀጥታ ቢቀበሉት ይህን የመሰለውን የቸርነት ሥራ ለመሥራት ያስችልዎት አልነበረምን ?

መልስ ፡ በመሠረቱ ቸር አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ፡ ይሁን እንጂ በተባለውም ዓይነት ቢፈጸም አድልዎን ማስከተሉ አይቀርም በመንፈሳውያን አባቶችም መካከል አድልዎ መኖር የማይገባውና ፈጽሞ የተወገዘ ስለሆነ አንድ ሰውም

ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ሊገዛ ስለማይችል ደመወዜን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተሻለ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ለተጠቀሰውም ሁሉ ነገር ቢሆን ከላይ እንደ ተገለጸው ለመንበረ ፓትርያርኩ የክብር መጠበቂያ ሲባል ልዩ ወጭ ስለአለ ችግር የለም፡ በዚያውስ ላይ ከአንድ መንፈሳዊ አባት መንፈሳዊ በረከት እንጅ ወቅርቅና ብር ይፈለጋልን ?

ጥያቄ ፡ ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ደመወዝዎ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቢውል የተሻለ መሆኑን ከቅዱስነትዎ መልሶች ለመረዳት ተችሏል ሆኖም በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ብዙ ዓይነት አገልግሎቶች እንዳሉ ቅዱስነትዎ ያውቀዋል ታዲያ ደመወዝዎ የተፈቀደው እንዴት ላለው አገልግሎት ነው ?

መልስ ፡ የቤተ ክርስቲያን ዋና ተግባር ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋትና ካህናትን ማሠልጠን ነው የተመሠረተችበትም ዋና ዓላማ ይኸው ነው ፡ ስለዚህ የእኔም ደመወዝ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ስፈቅድ ዋና ምኞቴና ፈቃዴ ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያና ለካህናት ማሠልጠኛ ፕሮግራም እንዲመደብ ነው ፡ የአስተዳደሩም ክፍል ምኞቴንና ፈቃዴን ተቀብሎ ከተጨባጭ ሥራ ላይ እንደሚያውለው አልጠራጠርም ቊጥጥርም የማድረግ ኃላፊነት አለብኝ ።

ጥያቄ ፡ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ቅዱስነትዎ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፫ኛው ፓትርያርክ ሲሆኑ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ውስጥ ይህ ዓይነቱ በገንዘብ ፍቅር አለ መጠመድ ለመጀመሪያ ጊዜ መሰማቱ ነው መቼም ይህ የቅዱስነትዎ አባታዊ አርአያነት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከፍተኛ ትምህርት ነው ፡ በዚህ ዓይነት ሌሎቹም መንፈሳውያን አበው እንዲተባበሩዎት ምኞት አለዎትን ?

መልስ ፡ የሁላችንም መሠረታዊ ዓላማ ይኸው ስለሆነ የእኔ መሰሎች የሆኑ ሁሉ ቢተባበሩ ቤተ ክርስቲያናችን የተሻለ እርምጃ እንደሚኖራትና መንፈሳዊው ተግባራችን ሁሉ የተቃና እንደሚሆን አልጠራጠርም ፡ ሆኖም ይህ ዓይነቱ ተግባር በእግዚአብሔር ጸጋ ከራስ ሕሊና በመነጨ በራስ በጎ ፈቃድ የሚፈጸም እንጅ በትእዛዝና በምክር ሊከናወን ስለማይችል ማንም በማንም ላይ እንዲፈርድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ አይደለም ።



# መልካም አርአያነት ፤

ለክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ
አዲስ አበባ ፡

እንኳን ለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ ልደት በሰላም አደረሰዎ ።

ከኅብረተ ሰብ ጉዳይ የግለሰብ ጉዳይ መቅደም እንዳለበት እሙን ነው ። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የግል ጉዳይ የጋራ የሚሆንበት ሁኔታ አለ ። የተሟላ የኑሮ አቋም የሌላቸው ግለሰቦች መልካም ኅብረተሰብን ሊገነቡ አይችሉም ። በሌላ በኩል ደግሞ ዓላማውን የለቀቀና የተዛባ የኅብረተሰብ አቋም ያለው ድርጅት ችግረኛና ጎስቋላ ግለሰቦችን ይፈጥራል ። የሁለቱም ጉዳይ አሳሳቢ ስለሆነ በተዋሕዶ ተመልክተን መፍትሔውን መሻት ይኖርብናል ። ስለዚህ ነው በዚህ ደብዳቤ ውስጥ የግልና የጋራ ጉዳዮችን ይዤ የቀረብኩት ።

እንደሚያውቁት ሁሉ በሰበካ ጉባዔ ሥራ ላይ ከተሠማራሁ ጥቂት ወራት አልፈዋል ። ነገር ግን ስለተዘዋዋሪ ጓድ የተጠየቀውም ሆነ ለሥራ ማስኬጃ እንደዚሁም ለደመወዝ እስካሁን ድረስ የተሰጠኝ ነገር የለም ። እንደኔም ተመሳሳይ ችግር ያጋጠማቸው አሉ ።የችግሩንም መንሥኤ የጊዜው መሳይ ማርክሲስት እንደምታ ወይም ይትበሐል ስለሚመስልብኝ የነገሩንም ሐቀኛነት ስለምጠራጠረው ጉዳዩን ለአጥኒዎችና ለመርማሪዎች ትቸዋለሁ ።

የሆነ ሆኖ በእኔ አስተያየት ማንኛችንም ብንሆን ሳናውቀውም ሆነ አውቀነው ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የቤተ ክርስቲያን ችግር ተሳታፊዎች ነን ስለዚህ ቢመጀመሪያ በራሳችን ፍርድ አሳልፈን እርምጃ ወስደን ወደ ሌላውደግሞ መተላለፍ ይገባናል ። ይህንን ብናደርግ እውነትን አንበድልም ፍርድንም አናጓድልም ።

ከላይ የተጠቀሰውን ፍሬነገር ያወሳሁበት ምክንያት ስለደመወዜ ሁኔታ ለመግለጽና እኔም ስለዚሁ የወሰድኩትን አነስተኛ እርምጃ እንደሚከተለው ለማስረዳት አስቤ ነው ።

በመጀመሪያ ቤተ ክህነት ከገባሁበት ጊዜ ማለት ከነሐሴ ወር ፲፱፻፷፰ ዓ/ም እስከ ታህሣሥ ወር ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ድረስ ያልተከፈለኝ ደመወዜ አሁን በቅርቡ መፈቀዱን ከሒሣብ ክፍል ስለተነገረኝ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁሉ አመሰግናለሁ ። ይኸው የተፈቀደልኝ ደመወዜ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይከፍለኝ በነበረው ልክ መሆኑንና ይህም ገንዘብ ከቤ/ክ ገቢላይ የተወሰደ እንጂ ከዩኒቨርስቲው የተዛወረ በጀትአለመሆኑን ተረድቻለሁ። ይህም ሁኔታ የግልንና የጋራ ችግሮችን አስከትሏል ፕሮብሌሙም ከኔ ጋር ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን ሁሉ ይመለከታል ።

መፍትሔውም በቀላሉ የሚገኝ ወይም በመጠባበቅ አውቆ የሚመጣ ነገር አይደለም ። በሽታውን ያልተናገረ መድኃኒት አይገኝለትም ። ቤተ ክህነት በሽታዋ ራስ ምታቷ ይገለጽመድኃኒቱም ይፈለግ ለዚህም የሐኪሙና የወጌሻው የማያቋርጥ ትግል ያስፈልጋል ። የሁላችንንም መንፈሳዊ ተጋድሎ ይጠይቃል ። «ነገርግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» እንደተባለ በመጀመሪያ ቤተ ክህነታችን ሃይማኖታዊ ድርጅት መሆኑ ይታመንበት አንድ ሐዋርያዊ ዓላማ እንዲኖረው ይደረግ ፤ በአንዲት የቤ/ክ/ ሕግ ይመራ በሰበካ ጉባኤ ሕዝበ ክርስቲያኑን የሚያደራጅ ዘመቻ በኅብረት ይደረግ ሐዋርያዊ አገልግሎት ይስፋፋ ይህ ዓይነቱ ነገር ከልብ ታምኖበት በሥራ ሲተረጎም ነው ቤተ ክርስቲያናችንና አገልጋዮቿ የእድገትና የሕይወት ተስፋ ለማግኘት የምንችለው ። እስከዚያው እያንዳንዱ ሊያደርግ የሚገባውንና የሚችለውን ያድርግ ። እኔም ከሥራ ጓዶቼ ጋር ላደርገው የሚገባኝን በእግዚአብሔር ርዳታ ለማድረግ እስክችል ድረስ ለጊዜው ከደመወዜ ላይ የሚከተለውን አነስተኛ ቅናሽ ለማድረግ ወስኜአለሁ ።

፩ኛ/ ከነሐሴ ወር ፲፱፻፸፰ ዓ/ም ጀምሮ የተፈቀደልኝ የደመወዝ ልክ ፰፻፲ (ስምንት መቶ አሥር ብር) መሆኑ ቀርቶ ፭፻፹፭ (አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) ብቻ እንዲሆን ፤

፪ኛ/ ተቀናሹ ፪፻፳፭ (ሁለት መቶ ሃያ አምስትብር) በየክፍለ ሀገሩ እየተዘዋወሩ ሰበካ ጉባኤን ለሚያቋቁሙና ለሚያጠነክሩ ምንም ወይም ትንሽ ደመወዝ ላላቸው ሰባክያን ወንጌል አበል እንዲመደብ በትሕትና አሳስባለሁ ።

በክርስቶስ ሰላም

አበራ በቀለ



# ተ ና ገ ሩ አ በ ው

ከማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ የወጣቶች መ/ ማኅበር

ከዋለ ይሁን ክንዴ

ተናገሩ

ተናገሩ አበው የጥንቱ ፤
ድሮ እንዴት ነበር ሥርዓቱ?
ሥልጣኔ በሌለበት በዚያ ጨለማ ፤
መኪና መፈጠሩ ሳይሰማ ፤
አገር በሰፊው ሳይለማ ፤
አበው ኑሮ እንዴት ነበር የሚስማማ ?
በጥቂት ቀናት ሠርታችሁ
በትንሹ ዘር ዘርታችሁ ፤
ዝናም ከሰማይ ዘንቦላችሁ
ዘሩ ፍሬ ሲሆንላችሁ
ስትከምሩ አጭዳችሁ ።
እጅግ ሲበዛ ምርታችሁ
እንዴት ነበረ ደስታችሁ?
አበው በዓላትን ስታከብሩ
ስትጾሙ ስትጸልዩ ስትዘምሩ
እየደገሳችሁ ለሌላው ድሀ ስትቸሩ
እህል አልቆባችሁ ጦም እስታድሩ
አበው በዚያ በደጉ ዘመናችሁ
እንግዳ አክባሪ የሆናችሁ
ሰውን ስታምኑ ከልባችሁ
መንደገኛውን ጠርታችሁ
ወደ ቤታችሁ አስገብታችሁ
ያላችሁን አብልታችሁ አጠጥታችሁ
በሞቀ ውሃ እግሩን አጥባችሁ
መኝታችሁን ለእንግዳው ለቃችሁ
መሬት ስትተኙ ቅርም አይላችሁ ፤
ጋሻና ጦር ሰይፋችሁን ታጥቃችሁ
ከፈረስ ላይ ጉብ ብላችሁ ፤
ሽምጥ ስትጋልቡ ፎክራችሁ
ጠላትን ስትገጥሙ ደፍራችሁ
እንዴት ቆራጦች ነበራችሁ !
ለኢትዮጵያ አገራችን እንሞታለን ፤
ለሃይማኖታችን እንሰዋለን
ለወገኖቻችን እናልፋለን
ብላችሁ ስትነሡ ለመዋጋት
አዝማድና ልጆች ደግሞም ሀብት
እሊህን ሁሉ በመሰዋት
ቁልቁል ወርዳችሁ ወጥታችሁ ዳገት ፤

ፊት ለፊት ስትገጥሙ ጠላት
ከተፋፋመው ጦር ከዚያ እሳት
ዘላችሁ ስትገቡ በድፍረት
ትንሽ ስንኳን አልተሰማችሁም ፍርሃት ፤
ቤታችሁን ሲያፈርስ በታንክ
ቦንብና አዳፍኔ ከወደሰማይ ሲላክ
ጠላትን በጦር አብርራችሁ
እንዴት ነበር የማረካችሁ?
ቦንብ ከሰማይ ጥይት ከምድር
እናንተን ለማጥፋት ሲወራወር
አገርን ለመግዛት ሲጣጣር
ጭራሽ ለጠላት ሳትበገሩ
ጋሻ መከታችሁ ጦርን ስትወረውሩ
በጎራዴና በካራ አንገት አንገቱን ስትመትሩ
ታንክንም ስትማርኩ በበትሩ
አበው የኃይላችሁ ምንጭ ምን ነበር ሥሩ
ዛፉ አራዊቱ የአገራችሁ
በግ በሬው ሲያልቅባችሁ
ወገን ሲረፋረፍ ከጎናችሁ
ግፉ አላስችል ብሎ በዝቶባችሁ
በሀገራችሁ ላይ ተሰዳችሁ
ለወገናችሁ ብላችሁ
ያን ለመመለስ ምን መከራችሁ?
ታንክ መትረየስ አዳፍኔ መድፍ
አይሮፕላኑ በሰማይ ላይ ሲንሳፈፍ ፤
ቀን በፀሐይ ሌት በቁሩ
በበረሀ በውሀ ጥም ስትከሩ
በአገር ዋዛ የለም ብላችሁ
ገደል ለገደል ተባራችሁ
በሃይማኖት ድል የሞታችሁ
ማን ነበር ለዚህ ሁሉ ረዳታችሁ ።
አበው ይህን መከራ ስታሳልፉ
አንድ ቀን እንኳን ሳትሰንፉ
እስከመጨረሻው ስትዋጉ ሳታርፉ
ጠላትን መለሳችሁ የመጣባችሁን በግፉ
ስለ አገራችሁ ሰውታችሁ ዕድሜአችሁን
ለትውልድ ትታችሁ ሥራችሁን
አበው ፤ እናንተም አፈር ሆናችሁ ዋ ሰው መሆን ! !



# የትኛውን ልምረጥ ?

ከወይዘሪት ፀሐይ ገብረ እግዚአብሔር

አባቴም ይለኛል ሴት ልጅ አትመርጥም ፤
እናቴም ትላለች ሴት ልጅ አትመርጥም ፤
መብቱ የወላጅ ነው መምረጥም መዳርም ።
አሉኝ ወገኖቼ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ፤
እኔ ለእኔ ምርጫ እንዴት ነው የማንሰው?
ምርጫ እችል ከሆነ ምክራችሁ ይድረሰኝ ፤
ውድቀቴ አጉል ሆኖ እንዳያሰድበኝ ፤

የትኛው ሰው ይሆን ወንድም የሚሆነኝ ለትዳር ጓደኛ ፤
የድሃው ልጅ ይሆን የሚቀምሰው ያጣ የዚያች ችግረኛ?
የቀጥቃጭ ይሆን የባለ መክሊቱ የዚያ ያንጥረኛ ?
ወይስ የዘላኑ አገር ላገር ዟሪ እግረ በረኸኛ?

የትኛውን ልምረጥ እስኪ ምክር ስጡኝ ፤
እንደኔ ለትዳር የሚሆን ሰው ቢገኝ ፤
ያንን ልምረጥ ይሆን ለሁሏም የሚሞት ለሁሏም አለሁ ባይ ፤
ቅልስልስ አይን አፋር አውቆ ጨዋ መሳይ ።
በመንገድ ያያትን አድርሶ የሚመልስ ፤
የሴት ጭራ ይዞ መንደር የሚያዳርስ ።
ሽንገላን የሚችል ባይን ወረቱ ለዛ ፤
እሱ ይሆን ታድያ ለሦስቱ ጉልቻ በፍቅር የሚገዛ?

ወይስ ሌላ ልምረጥ በትምህርት ይዞታው በውቀት የረቀቀ ፤
ጨውነትን ለብሶ ጥበብን ያጠለቀ ፤
አንዴ ከወደደ የማያውቀው ወረት ፤
እሱን ልምረጥ ይሆን ለቤቴ ባለቤት?
ወይስ በወገኑ በክብር የነጎደ ፤
ገንዘብ እንደልቡ መርጨት የለመደ ።
በተብለጭላጭ ጌጥ የሚሽሞነሞነው ፤
ያልተቆነጠጠ ተግሳጽ ያልጎበኘው ።
እስከ መጨረሻው የሚሆን ቁራኛ ፤
እሱ ይሆን ታድያ የኑሮ ጓደኛ ?

ከሩቁ ጠልቄ እንዲህ የማስበው ፤
የልጆቼን ኩርኩም እንዳላይ ብዬ ነው ።
ታድያ የቱን ልምረጥ ምን መከራችሁኝ ፤
ለቤቴ ባለቤት ለልጆቼም አባት እንፈልግ አፋልጉኝ ።

ከዚያ ልምረጥ ይሆን ከዚህኞቹ ሰፈር ከጉረኞች አምባ ፤
ከነብር ትራሱ ከነወሬ አራቂ ከነብር ወሸባ ።
የተበታተነን ቤተሰብ ሰብሳቢ ፤
ይገኝ ይሆን ከዚያ ለትዳሩ አሳቢ

ወይስ ሌላ ልምረጥ ከከተማው ውጭ አፈር ከሚገፋው፤
በዝናብ በውርጭ በፀሐይ ተቃጥሎ ኑሮን ካጣፈጠው ፤
እሱኛውን ልምረጥ? ሁሉ ለኔ የማይል ለትዳሩ ሙት ነው?

ወይስ የቀጥቃጭ የሸክላ ሰሪው ልጅ ለፍቶ በላተኛ ፤
ተግባሩ ተጠልቶ ጋብቻ ተነፍጎት የሆነው ብቸኛ ።
ባለ ሙያውን ሰው የጅስራ አዋቂ ፤
ስሙን ሲለውጠው አንዳንድ ወሬ አራቂ ።
«ጠቢብ» በሚል ፈንታ «ጠይብ» ባይ ስም ሰጥቶ ፤
ቡዳ ነህ ይለዋል «ቢ» ን-በ«ይ» ተክቶ ።
ታድያ እሱን ልምረጠው? ምን መከራችሁኝ
የልጆቼ ነገር በጣም አሳሰበኝ ፤

ያንን ልምረጥ ይሆን የሸማኔውን ልጅ ቁቲት ቋጣሪውን የዚያ ጥበበኛ
ሌሊቱን ሲያዳውር ቁጭ ብሎ የሚያድር እንቅልፍ የማይተኛ ።
ያገር ባህል ቅርሱ ካገር እንዳይጠፋ ፤
ዘወትር የሚያስብ ከልብ የሚለፋ ፤
እሱንስ ብመርጠው አገኝ ይሆን ተስፋ?

ወይስ ሌላ ልምረጥ ከተማረው ቡድን ፤
ከነፕሮፌሰር ከዶክተሮች ወገን ።
ወይስ ከዘማቹ ወይ ከወዝ አደሩ ፤
መዋስ ከከተሜው ደግሞ ከገጠሩ ።

የትኛውን ልምረጥ ከነዚህ መሐከል ፤
ልጅ የማስታቅፈው ቁርጥ እርሱን መሰል ፤

አይን አዋጅ ሆነብኝ የወረት ቅብጥብጥ ፤
የትኛውን ትቼ የትኛውን ልምረጥ?